# ኪ ዳ ና ች ን
# KIDANACH'N

ልዩ ዕትም  መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ ምሕረት

Special Edition  Meskerem 1, 2015 A.D
(September 11, 2022)

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥
ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና
የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡
በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።

Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"
to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom
of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy
Covenant with God;
and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

# የ፪ሺ፲፭ (፳፻፲፭) ዓመተ ምሕረት፡
# ቀን መቍጠሪያ

## 2015 (2022-2023 Gregorian) Calendar

አዘጋጅ፦ ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (ቄስ)፡ ንቡረ እድ ዘአኲስም ጽዮን።

ንድፍ፦ ኪዳናዊ ዮሓንስ ደጉ ጥሩነሽ።



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ-ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
God The Son Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melke-Zedeqthe Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ

Ethiopia Reaches out Her Hands to God
Goddess The Mother Virgin Mary
Mother of Our Messiah and Our Holy Mother
Queen of Sovereigns of Zion and Ethiopia

# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት

# ልዑል እግዚአብሔር፡

## ከዘመነ ማርቆስ ፡ ወደዘመነ ሉቃስ አሸጋግሮ፡

## የኢትዮጵያን የነጻነት ህልውና በዓላችንን፡ ፯ሺ፭፻፲፫ኛ ዓመት፥

እና

## የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ ፪ሺ፳፮ኛ ዓመት፥
## የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ፪ሺ፲፫ኛ ዓመት፡
## የትስብእት ልደታት በዓሎቻችንን፡ ለማክበር ለበቃንበት፡
## ለዓዲሱ፡ የ፪ሺ፲፫ (፭፻፲፫) ዓመተ ምሕረት፡
## እንኳን አደረሰን!

\+ + +

# ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ፡፡

፩ኛ፡- ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡ "**ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!**" በሚለው፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም፥ ፳፻፱ ዓ.ም. ፥ ፳፻፲ ዓ. ም. እና ፳፻፲፩ ዓ.ም. በታተመው መጽሓፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሓተታዎች መሠረት በማድረግ ነው።

፪ኛ፡- "**በዘንዜከር**" በተባለው፡ የየዕለቱ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቍጥሮች ጋር የሚደመረው **የ፳፻፲፫ቱ (የዕሥራ ምእት ዐሠርቱ ወአምስቱ) [የ፪ሺ፲፫ኛው] ዓመተ ምሕረት፡ ዓበቅቴው፡ ፱ [ዘጠኝ]፥ መጥቅዑ፡ ፳፩ [ኻያ አንድ]** ኾኗል።

፫ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ ሌላ መግለጫ ካልተሰጠ በቀር፡ **ዕረፍታቸውን፥ የኣኀዞቹ** [የቍጥሮቹ] የተለያዩ ቀለማት ደግሞ፡ ከዚህ የሚከተሉትን ኣብነቶች ያመለክታሉ፡-

ኣ. ቀዩ፡ **ዕለተ-ሰንበትን** ["ቅዳሜ" ስትባል የኖረችውን]፥ **ዕለተ-ሰንበት ዝልፍትን** [በ"እሑድ" የቀጠለችውን "ዘላለማዊቷን ሰንበት" (ዝልፍት)]፥ ዓበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የፍስክ ዕለታትና ሳምንታት፣

በ. ኣረንጓዴው፡ ንኡሳን በዓላትን፣

ገ. ሰማያዊው፡ የኣጽዋማት ቀኖችንና ሳምንቶችን፣

ደ. በቀን መቁጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ ያሉት የክብ ምልክቶች ብዛት፡ በማውጫው ውስጥ የተገለጹትን፣ በእያንዳንዱ ቀናት ውስጥ ያሉትን የበዓላትና የኣጿማት ብዛት የሚያሳዩ ናቸው።

፬ኛ፡- **መስከረም ፩ ቀን፡-**

❖ምናልባት፡ በእየራሳችን ድክመትና ስሕተት፥ ጒድለትና ጥፋት፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊም ኹለንተናችንን፡ ያሳደፍንበትና ያበላሸንበት፥ ያሰነካከልንበትና ያስረጀንበት፡ ኣካላዊና ባሕርያዊ የኾነ፡ የኣምልኮ ምንዝርና ግብር ቢኖር፡ ያን ኹሉ፡ የርኵሰትና የልክስክስነት ግብስብስና ዝባዝንኬ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ፈጽመን፡ ከሰውነታችን በማስወገድ፡ ወዲያ ኣውጥተንና ኣሽቀንጥረን ጥለን፣ ኹለንተናችንን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ኣንጽተን ያደስንባት፣

❖ከዚህም ጋር፡ ቅዱስ ቁርባናችን በኾነው፡ በሥጋ ወደሙ፡ ኹለንተናችንን ቀድሰን፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ለእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና ለልጇ ለወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የልደታት በዓላችን ክብር ያበቃንባት፣

❖ሰላማችንን ያስገኘልን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ድኅነትን [መዳንን] ካስገኘችልን፡ ከእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ በቅዱሱ ኪዳን የተጐናጸፍነውንና የተቀዳጀነውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደዓዲስ ተኧሚና ተሸላሚ ባለድል የተቀበልንባት፣

❖ከኣሮጌው፡ ወደዓዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ትንሿን ትርፍ የጳጒሜን ወር፡ በንስሓ፥ በጋድ ጾምነትና ንኡስ ሱባዔነት፡ የምስጋና ጾምና ጸሎት አድርገን ያሳለፍንባት መኾኗ ሊዘከር [ሊታሰብ] ይገባል።

፭ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው፡ እያንዳንዱ ሠንጠረዥ ግርጌ፡ ለየወሩ የተመደቡ ምንባቦች ተሰናድተዋል። እነዚህ ምንባቦች የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን፥ እንዲሁም፡ በየሰንበቱ፥ በሌሎቹም፡ የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ፡ ከቃለ-እግዚአብሔር ዝክረ-ነገር ላለመራቅ

እንደሚቻል በመገመት ነው። መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም፤ አልተካተተም።

፮ኛ፡- ጾሙና ጸሎቱ፥ የሱባዔው ጭምር፥ ምንባቡም፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም፡ በኅብረት በመሰባሰብ ሊካኼድ ይቻላል።

፯ኛ፡- ይህን የቀን መቍጠሪያ፣ እንዲሁም፡ "**አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!**" በሚል፡ ዓቢይ ርእስ ሥር፡ "**አንደኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ!**"፥"**ኹለተኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ!**" እና "**ሦስተኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውቀት ፍለጋ!**" በተጨማሪም፡ በኢትዮጵያኛ እና በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ፡ «**የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ ለኢትዮጵያ ሕፃናት፤ "አንደኛ እና ኹለተኛ መጻሕፍት"**» የሚል አርእስት ያላቸውን ዕትሞች እና እየታተሙ ያሉትን፥ ደግሞም፡ "**ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት።**" ከእነዚህ በተጨማሪ፡ "**ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት**" በሚል አጠቃላይ አርእስት ሥር፡ "**አንደኛ መጽሐፍ**"፥ "**ኹለተኛ መጽሐፍ**" እና "**ሦስተኛ መጽሐፍ**" ተብለው፡ በተከታታይ የወጡትን፥ እንዲሁም፡ ቀደም ብለው፡ "**ምናሴ፡ የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!**"፥ "**ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!**"፥ "**ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!**" እና Ethiopia: The Classic Case በሚሉ አርእስት፣ እነዚህ ኹሉ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ አንዳንዶቹም፡ ለኹለተኛ፥ ለሦስተኛና ለአራተኛ ጊዜያት ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን፥ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት፡ የኀዋ ሰሌዳችንን መኀብኘት፥ እንዲሁም፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።

**አሳታሚ እና አከፋፋይ**

Publisher & Distributor

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።**

**Ethiopia: The Kingdom of God.**

መልእክት ሣጥን ቍጥር፡ ፰፻፲፪። P. O. Box 812.

**ስልክ ቍጥር**፡- 0፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና 0፲፩-፰-፵-0፰-፴፬፤

Tel.፡- (011-4-16-18-85 & 011-8-40-08-34)፤

**የኪስ ስልክ ቍጥር**፡- 0፱፻፵፬-፲ ፳፫ ፷፰ እና 0፱፲፩-፷፰ ፵፬ ፶፪፤ እና 0፱፲፩-፷፩ ፲፭ ፹፫ እና 0፱፳-፹፬ ፹፰ ፲፯ እና 0፱፳፱-፲፯ ፵፬ ፶፭

Cellphone (0944-10 23 68 & 0911 68 44 52 & 0911 61 15 83 & 0920 84 88 17 & 0929 17 44 55)

ዓዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ። Addis Abeba, ETHIOPIA

ወይም or

**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~**

**USA. Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**

Cellphone: 202-763-0903

Email: info@ethkogserv.org Web Site: www.ethiopiathekingdomofgod.org

Facebook (ፌስ ቡክ): ethiopiathekingdomofgod

**+ + +**

## ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2022). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 11 የድንግል ማርያምና የኢየሱስ መሲሕ ልደት ●●●●●● | ፪ 12 ● | ፫ 13 ● | ፬ 14 | ፭ 15 ●● | ፮ 16 ● | ፯ 17 ●● |
| ፰ 18 ግዝረት ● | ፱ 19 | ፲ 20 ● | ፲፩ 21 ● | ፲፪ 22 ● | ፲፫ 23 | ፲፬ 24 |
| ፲፭ 25 | ፲፮ 26 ደመራ ●● | ፲፯ 27 መስቀል ● | ፲፰ 28 ● | ፲፱ 29 | ፳ 30 ● | ፳፩ 1 ፍልሰተ ዕርገት ●● |
| ፳፪ 2 | ፳፫ 3 | ፳፬ 4 ● | ፳፭ 5 ●● | ፳፮ 6 ጽጌ ● | ፳፯ 7 | ፳፰ 8 ● |
| ፳፱ 9 የጽጌ ማሕሌት | ፴ 10 | **ማስታወሻ፡-** *ከቅዱሱ ኪዳን፡ ለሰው ዘር፡ የመጨረሻ፡ የማንቂያ እና የማስጠንቀቂያ ደወል፡ በኒው-ዮርኩ የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. የቃጠሎ ግድያና ዕልቂት የተሰማባት፡ መስከረም ፩። (9/11) | | | | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

፩ የድንግል ማርያም እና የኢየሱስ መሲሕ ልደታት
† የኢትዮጵያ ነጻነት † ኪዳነ አዳም ወሔዋን † ቅዱስ ራጉኤል ሊቀ መላእክት † ቅዱስ ዮሓንስ መጥምቅ † በርተሎሜዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ።

፪ ዮሓንስ መጥምቅ።

፫ ገዳማዊ ኣንበስ ኢትዮጵያዊ።

፭ ሄሮድስ የፈጃቸው ሕፃናት † የኣሕመድ ግራኝን ወረራ በሃይማኖት ተቋቁሞ የተጋደለ፡ ኣጼ ንብለ-ድንግል።

፮ ኢሳይያስ ነቢይ።

፯ ኢትዮጵያዊቷ ኤልሣቤጥ፡የመጥምቁ ዮሓንስ እናት † መናኔ-መንግሥት፡ ኣጼ ተክለ-ሃይማኖት።

፰ ግዝረተ-ኢየሱስ።

፲ ኣጼ መስቀል። ግማደ-መስቀሉ፡ በ፲፬ኛው ፻ ዓመት፡በ፩ኛ ኣጼ ዳዊት፡ወደኢትዮጵያ ገባ።

፲፩ ኣጼ በካፋ፡ ስመ-ጥሩው ምሁር መሪ።

፲፪ ስለንስጥሮስ ኑፋቄ፡ የ፪፻ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኤፌሶን

፲፮ ደመራ (ለመስቀል የችቦ እሳት: የዛፍ ኣጠናዎችን መደማመር) † ኪዳነ ኖኅ

፲፯ በዓለ መስቀል።ኢየሱስ መሲሕ የተሠዋበት እውነተኛው መስቀል ተገኘ።

፲፰ ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኤዎስጣቴዎስ፡ ስለቅዳሜ ሰንበትነት ረታ።

፳ የኢትዮጵያ እግዚአብሔር መንግሥት ምስክር፣ ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (የኣኵስም ንቡረ-እድ)።

፳፩ የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰተ ዕርገት † የኢየሱስ መሲሕ ዜና መስቀል፡ በግሼን ማርያም የሚነገርበት።

፳፬ ኪዳነ መልከ ጼዴቅ።

፳፭ ዮናስ ነቢይ † የክረምት (የዝናም) ወራት ማብቂያ።

፳፮ የመፀው (የጽጌ= የአበባ) ወራትና የጽጌ ማሕሌት መግቢያ።

፳፰ ኪዳነ ኣብርሃም።

**"ወፈለግ ይወጽእ እምቅድሜሁ፡ ከመ ይሥቅያ ለገነት፤ ወእምህየ ይትፈለጥ፡ ለአርባዕቱ መአዝነ ዓለም። ...ወስሙ ለካልእ ፈለግ፡ 'ግዮን'፤ ወውእቱ ዘየዐውድ ኵሎ ምድረ-ኢትዮጵያ። ...ወነሥአ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው ዘገብሮ፤ ወሤሞ ውስተ ገነት፡ ከመ ይትገበራ፤ ወይዕቀባ።** ገነትንም ያጠጣ ዘንድ፡ ከፊትለፊቱ፡ ወንዝ ይወጣ ነበር፤ ከዚያም፡ ወደአራቱ የዓለም ማእዘኖች ይከፈላል። ...የኹለተኛውም ወንዝ ስሙ፡ 'ግዮን' ነው፤ እሱም፡ የኢትዮጵያን ምድር፡ ዙሮ የሚያጠጣ ነው። ...እግዚአብሔርም፡ የፈጠረውን ሰው ወስዶ፡ ያርሳት፥ ይቆፍራት፥ ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ፡ በገነት ላይ ሾሞ፡ በዚያ ኣኖረው።" [ዘልደት (ዘፍጥ.) ፪፥ ፰-፲፯።]

| የመስከረም ወር ምንባብ፡- | ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ] እና መጽሓፈ ጥበብ። |
|---|---|

## ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of T'q'mt (Oct-Nov., 2022). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሐሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ:-** | | ፩ 11 | ፪ 12 ● | ፫ 13 | ፬ 14 ● | ፭ 15 |
| ፮ 16 የጽጌ ማሕሌት ●● | ፯ 17 | ፰ 18 | ፱ 19 ● | ፲ 20 በዓተ-መቅደስ ●●●● | ፲፩ 21 ጾመ-ስደት ● | ፲፪ 22 ●● |
| ፲፫ 23 የጽጌ ማሕሌት | ፲፬ 24 ●●● | ፲፭* 25 ● | ፲፮ 26 | ፲፯ 27 ●● | ፲፰ 28 | ፲፱ 29 ● |
| ፳ 30 የጽጌ ማሕሌት | ፳፩ 31 | ፳፪ 1 ● | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 |
| ፳፯ 6 የጽጌ ማሕሌት | ፳፰ 7 ●● | ፳፱ 8 | ፴ 9 | **ማስታወሻ:-** | | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

* በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የመጨረሻው ንቡረ እድ ዘአኵስም ጳዮን የኾነው፡ ኪዳናዊ ቄስ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ፡ ዕረፍቱ፡ በመስከረም ፳ ቀን፤ ፳፻፲ ዓ.ም. ፤ በዓለ ሽኝቱ [ግብዓተ መሬቱ] ደግሞ በጥቅምት ፲፭ ቀን፤ ፳፻፲ ዓ.ም. በቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ርዕሰ አድባራት ተፈጸመ። ይህ ዕለት፥ መንፈስ ቅዱስ ባወቀ፡ ከ፵ ዓመታት በፊት፥ በጥቅምት ፲፭ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ.ም.፥ ንቡረ እድ ኤርምያስ፡ በቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት የአገልግሎት ዘመኑ፥ ራሱ ያዘጋጀው የሰበካ ጉባዔ መተዳደሪያ ህግና ደንብ ቃለ ዐዋድ፡ በነጋሪት ጠማር የታወጀበት ቀን ነው። በዚህም ምክንያት፡ ከ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. የአብዮትና የክህደት ዘመን ጀምሮ፡ እውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ህልውናዋ፡ በሕያውነት የመቀጠሏ መለኮታዊ ማረጋገጫ፡ ኩነተ ሥርዓት የተጀመረበት ቀን ኾነ።

፪ ገዳማዊ ሕርያቆስ፡ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ ።

፬ አጼ አብርሃ ወአጽብሓ፡የቅዱሱ ኪዳን ክርስትናን፡ በኢትዮጵያ ያስፋፉ።

፮ ሐና ነቢይት፡የነቢዩ ሳሙኤል እናት † ገዳማዊ ጳንጠሌዎን ከ፱ ቅዱሳን ፩ዱ።

፱ አጼ ዳዊት የኢየሱስ መሲሕን ግማደ መስቀል፡ ከኢየሩሳሌም ያስመጣና "ዓባይን እገድባለሁ!" እያለ፡ በዚያ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን፡ ከእስላሞች ጥቃት ያዳነ።

፲ ኢየሱስ መሲሕ በ፫ ቀኑ፡በእናቱ ዕቅፍ ቤተ-መቅደስ የገባበት † በዓለ-ስምዖን † ሐና ነቢይት † አጼ ፋሲል፡ካቶሊክነትን ተቃውሞ፡ ተዋሕዶነትን ያጸና።

፲፩ የሕፃኑ ኢየሱስና የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስደት መታሰቢያ ጾም መግቢያ።

፲፪ ባለምሥራቹ ማቴዎስ፡ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ † ቅዱስ ድሜጥሮስ፡ የቀንና የዘመን አቈጣጠርን ያስተካከለ።

፲፬ ፊልጶስ ሐዋርያ፡ ኢትዮጵያዊዉን ጃንደረባ፡ አቤሜሌክን ያጠመቀ † ገዳማዊ ዘሚካኤል አረጋዊ፡ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ † ገብረ-ክርስቶስ።

፲፭ የኪዳናዊ ቄስ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (የአኵስም ንቡረ-እድ) የሽኝት በዓል (ግብዓተ መሬት) በቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ርዕሰ አድባራት።

፲፯ እስጢፋኖስ ቀዳሚው ሰማዕት፡የሹመቱ መታሰቢያ † ዲዮስቆሮስ ኢትዮጵያዊ፡ የግብፅ ሊቀ-ካህናትና የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳይ፥ የአኰቴተ-ቍርባን ቅዳሴው ደራሲ።

፲፱ አጼ ይምራሕ ቀዳሚዎቹን የእስልምና ስደተኞች በኢትዮጵያ አስተናግዶ የሸኘውና እነርሱ፡"ነጋሽ" የሚሉት፡ኢትዮጵያዊ ንጉሥ።

፳፪ ባለምሥራቹ ሉቃስ።

፳፰ አማኑኤል † ገዳማዊ ይማአታ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ።

"ወይቤሎ እግዚአብሔር አምላኩ ለኖኅ:- 'ጊዜሁ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በጽሐ ቅድሜየ፡ እስመ መልአ ዐመፃ ዲበ ምድር እምኔሆሙ፤ ወናሁ አነ እደመስሶሙ እምድር። ...ባእ አንተ፥ ወኵሉ ቤትከ፡ ውስተ ታቦት፤ እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ በቅድሜየ፡ በዛቲ ትውልድ። ...ወገብረ ኖኅ፡ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር አምላኩ። ...ወዐጸዋ እግዚአብሔር ለታቦት፡ እምአፍአሃ፤ ወኮነ ማየ አይኅ ላዕለ ምድር፡ ፵ መዓልተ፥ ወ፵ ሌሊተ፤ ወመልአ ማይ፤ ወአልዓላ ለታቦት፤ ወተለዓለት እምድር።" "እግዚአብሔር አምላኩ፡ ኖኅን፡ እንዲህ አለው:- 'በሰው ላይ፡ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ፡ በፊቴ ደረሰ! ከእነርሱ የተነሣ፡ በምድር ላይ የግፉ ጽዋ ሞልቷልና፤ እነሆ፡ እኔም፡ ከምድር አጠፋቸዋለሁ።...አንተን ግን፡ በዚህ ትውልድ መካከል፡ በፊቴ፡ እውነተኛ ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና፡ አንተ፡ ከቤተሰብህ ኹሉ ጋራ፡ ወደመርከብ ግባ!' ኖኅም፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ...እግዚአብሔርም፡ መርከቧን፡ በውጭ በኩል ዘጋት፤ በምድር ላይ፡ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት፡ የጥፋት ውኃ ዘነበ፤ ውኃውም መልቶ፡ መርከቢቱን አንሳፈፋት፤ ምድርንም ለቀቀች።" የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው፡ ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ የኢትዮጵያ [ቀይ] ባሕርን አቋርጣ፡ አራራት ተራራ ላይ ለማረፍ፡ ከኢትዮጵያ ተነሣች። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፮፥ ፩-፲፫፤ ፯፥ ፩-፳፬።)

| የጥቅምት ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሩት እና መጽሓፈ ሲራክ። |
|---|---|

# ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of H'dar (Nov.-Dec., 2022). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | | ፩ 10 | ፪ 11 | ፫ 12 |
| ፬ 13 የጽጌ ማሕሌት ማብቂያ | ፭ 14 | ፮ 15 በዓለ-ቍስቋም | ፯ 16 | ፰ 17 | ፱ 18 | ፲ 19 |
| ፲፩ 20 | ፲፪ 21 | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 ጸመ-ነቢያት | ፲፯ 26 |
| ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30 በዓተ-መቅደስ | ፳፪ 1 | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 |
| ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6 | ፳፰ 7 | ፳፱ 8 | ፴ 9 | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

- ፩ ነአኵቶ ለኣብ፡ መንግሥቱን፡በኢትዮጵያዊው የመልከ-ጼዴቅ ሥርዓት የመራ አጼ።
- ፭ ኣምላካችን ኢየሱስ መሲሕን ተሰቅሎ ሣለ፡ ጎኑን፡ በጦር የወጋና ኋላ ኣምኖ፡ በሰማዕትነት የተጋደለ ለንጊኖስ † የስደት ጾም ማብቂያ።
- ፮ ቍስቋም ሕፃኑ ኢየሱስ እና ቅድስት እናቱ፡ በስደት የቆዩባት የኢትዮጵያ ገዳም በዓል።
- ፰ አርባዕቱ እንስሳ። መንበረ ሥላሴን የሚሸከሙ ፬ቱ ሕያዋን ፍጡራን፡- ሰው፥ ላሕም፥ አንበሳና ንሥር።
- ፱ ስለአርዮስ ኑፋቄ፡የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኒቅያ።
- ፲፩ ቅድስት ሓና ኢትዮጵያዊት: የድንግል ማርያም እናት።
- ፲፪ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ-መላእክት † አጼ በእደማርያም ሃይማኖታዊው ተጋዳይ።
- ፲፫ አእላፍ መላእክት።
- ፲፬ በደርግ የዓመፅና የክህደት አገዛዝ፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ላይ፡ የግፍ ግድያ ተፈጸመ።
- ፲፮ የጾመ-ነቢያት መግቢያ።
- ፲፯ ዓዲስ ኣበባ ከተማ፡ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም. የተቈረቈረችበት
- ፲፰ ፊልጶስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።
- ፳፩ ሕፃን ማርያም፡በ፫ ቀኗ፡ በቤተመቅደስ የቀረበችበት † ማርያም ጽዮን †ኪዳነ ሙሴ †ማክዳ ንግሥትና ልጇ ምኒልክ።
- ፳፫ ቆርነሌዎስ ጻድቅ (የሓዋ. ምዕ. ፲)።
- ፳፬ ፳፬ቱ ካህናተ- ሰማይ።
- ፳፭ መርቆሬዎስ ሰማዕት።
- ፳፮ በናግራን (የመን)፡ ኢትዮጵያውያን/ያት ሰማዕታት። በዚያ፡ የኣጼ ካሌብ ድል † ኢየሱስ-ሞዐ ዘሓይቅ።
- ፳፯ ገዳማዊ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ፡ ዘደብረ-ቍንጽል።
- ፳፰ ገዳማዊ ሊቃኖስ፡ከ፸ኙ ቅዱሳን ፩ዱ።
- ፳፱ የሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስ ደቀ-መዝሙር፡ ቀሌምንጦስ † የሰማዕታት መጨረሻ ጴጥሮስ።
- ፴ ገብረ መስቀል (አጼ) በዘመኑ፡ የቅዱስ ያሬድ ሙያና የ፱ኙ ቅዱሳን ዜና የገነነበት † የጾመ-ነቢያት ማብቂያ።

**"ወመልከ-ጼዴቅ አምጽአ ኅብስተ፥ ወወይነ፤ ወካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል፤ ወንጉሠ ሳሌም ውእቱ። ወባረኮ ለአብራም፤ ወይቤሎ፡- 'ቡሩኩ አብራም ለእግዚአብሔር ልዑል፣ ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ! ወቡሩክ እግዚአብሔር ልዑል፡ዘአግብአ ለጻላእትከ፡ ውስተ እዴከ! ወወሀቦ አብራም፡ ዐሥራተ ዕድ፡ እምኵሉ።'** መልከ-ጼዴቅም፡ የኅብስትና የወይኑን ቍርባን ኣመጣ፤ እርሱም፡ የገናናው እግዚአብሔር አገልጋይ፥ የሳሌምም ንጉሥ ነው። አብራምንም፡- 'አንተ፡ ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው፡ ለገናናው እግዚአብሔር የተባረክህ ነህ! ጠላቶችህን፡ በእጅህ የጣለልህ ገናናው እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው!' ብሎ ባረከው። አብራምም፡ ከገንዘቡ ኹሉ፡ ኣሥራትን ሰጠው።" **የእስራኤል ልጆች ኣባት የኾነውን፡ ኣብርሃምን፡ ለመለኮታዊው የግርዛት ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የኢትዮጵያ ልጆች አጼ የኾነው፡ የዚህ፡ የኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ የክህነት ኣገልግሎትና ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፬፥ ፲፯-፳)**

| የኅዳር ወር ምንባብ፡- | ኦሪት ዘፀአት እና ትንቢተ ኤርምያስ። |
|---|---|

# ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Tah'sas (Dec., 2022-Jan, 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ ከተራ 8 ● | ማስታወሻ:- *ከተራ፡ ለጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ ውኃ፡ ከወንዝ ተወስዶ የሚከተርበት (የሚጠራቀምበት)። | | | | | ፩ ትስብእት 10 ●●●● |
| ፪ 11 | ፫ 12 በዓታ-ለማርያም ●●●● | ፬ 13 ● | ፭ 14 ● | ፮ 15 ● | ፯ 16 ጽንሰታ-ለማርያም ● | ፰ 17 ● |
| ፱ 18 ስብከት ● | ፲ 19 ● | ፲፩ 20 | ፲፪ 21 ● | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 ● | ፲፭ 24 |
| ፲፮ 25 ብርሃን | ፲፯ 26 | ፲፰ 27 ● | ፲፱ 28 ● | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 |
| ፳፫ 1 ኖላዊ ● | ፳፬ 2 ● | ፳፭ 3 ● | ፳፮ 4 ● | ፳፯ 5 ● | ፳፰ 6 | ፳፱ 7 ● |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

፩ በዓለ ትስብእት፡ ኢየሱስ መሲሕ የተፀነሰበት † ብሥራተ ገብርኤል †ኤልያስ ነቢይ †ቤትሳባ ኢትዮጵያዊት የሰሎሞን እናት።

፫ ሕፃን ማርያም፡ በስእለት፡ ለቤተ-መቅደስ የተሰጠችበት †ቅዱስ ፋኑኤል ሊቀ-መላእክት †ዳግማዊ ኣጼ ምኒልክ †ሁብተ-ጊዮርጊስ፡ አባ መላ።

፬ እንድርያስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።

፭ የቅዱሱ ኪዳን ማስጠንቀቂያ ኾኖ፡በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.፡ በክብር ዘበኛ ጦር አዛዥ የተመራው፤ ብዙ ደም ያፈሰሰው ያልጋ ግልበጣ ሙከራ።

፮ የዐዲስ ዓለም ማርያም ሰማዕታት ካህናት፡ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን የተሠየፉት።

፯ ፅንሰታ ለማርያም (ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት)።

፰ ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኪሮስ።

፱ ገዳማዊ በአሚን ኢትዮጵያዊ።

፲ በወሎ፡ደብረ እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ-እስጢፋኖስ፡በአሕመድ ግራኝ ጦር ተበዘበዙ።

፲፪ ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ሳሙኤል፡ የዋልድባው።

፲፬ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም.የፋሺስት ጣልያን አየር ኃይል በኢትዮጵያ ላይ፡ የመርዝ ጢስ ማዝነብ ጀመረ።

፲፰ በአኵስሙ ሊቀ-ካህናት እንበረም ወደ ግብፅ ተልኮ፡ ያልታሰበውን የግብፅን የጵጵስናን አገዛዝ ወደኢትዮጵያ ያመጣ ፍሬምናጦስ።

፲፱ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡፫ቱ ደቂቅን፡ከባቢሎን እሳት አዳነ።

፳፫ ኪዳነ ዳዊት።

፳፬ የእቲሳው እጨጌ ተክለ-ሃይማኖት ልደት።

፳፭ የመፀው (የጽጌ) ወራት ማብቂያ።

፳፮ የሓጋይ (የበጋ) ወራት መግቢያ።

፳፯ ኣጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ።

፳፱ የቅዱስ አጼ ላልይበላል ልደት።

፴ ከተራ*፡[የጋድ ጾም]።

ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ከባረከው በኋላ፡ እግዚአብሔር ተገልጦለት፡ **"አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣሪከ፡ ዘሖርኩ ቅድሜከ! አሥምር ቅድሜየ! ወኩን ንጹሓ! ወእሠይም ኪዳነ፡ ማእከሌየ ወማእከሌከ! ወአብዝኀከ ጥቀ! ...ወኢይሰመይ እንከ ስምከ 'አብራም'፤ አላ፡ 'አብርሃም' ይሰመይ! እስመ አበ ብዙኃን አሕዛብ ረሰይኩከ።** በፊትህ የኼድሁ ፈጣሪህ እግዚአብሔር፡ እኔ ነኝ! በፊቴ፡ በጎ ነገር አድርግ! ንጹሕ ኹን! በእኔ እና በአንተ መካከል ኪዳንን እሠይማለሁ! እጅግም አበዛሃለሁ!...እንግዴህም፡ ስምህ፡ 'አብራም' አይባልም፤ 'አብርሃም' እንጂ። ለብዙዎች አሕዛብ፡ ወላጅ አድርጌሃለሁና።" ያለው፡ ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው፡ ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ፡ ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን፡ በሚስትነት አግብቶ፡ **"ምድያማውያን"** የተባሉ፡ የኢትዮጵያን ልጆች በመውለዱ፡ ለኢትዮጵያዊነት፡ አንዱ አብነት ኾኗል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፯፥ ፩-፭፤ ፳፤ ፳፭።)

| | |
|---|---|
| የታኅሣሥ ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሳሙኤል እና ትንቢተ ሕዝቅኤል። |

# ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of TT'rr (Jan.-Feb., 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ 9 ጥምቀት | ፪ 10 | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13 | ፮ 14 |
| ፯ 15 አስተርእዮ ቅድስት-ሥላሴ | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20 ቃና ዘገሊላ | ፲፫ 21 |
| ፲፬ 22 | ፲፭ 23 | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28 |
| ፳፩ 29 አስተርእዮ-ማርያም መርዓዊ | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 | ፳፬ 1 | ፳፭ 2 | ፳፮ 3 | ፳፯ 4 |
| ፳፰ 5 የበዓለ ኢትዮጵያ መግቢያ | ፳፱ 6 በዓለ ኢትዮጵያ | ፴ 7 የበዓለ ኢትዮጵያ ማብቂያ | ማስታወሻ፡- | | | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

፩ ጥምቀት፤በዓለ አስተርእዮ † ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ [ባኮስ] † በቅዳሴ ጸሎቱ፡የጥምቀት ወንዝ የቆመለት የተጕለቱ ታቦት-ዋሻ ካህን፡ ትልቁ ቀሲስ ወልደ-ኢየሱስ።

፪ አቤል ጻድቅ።

፫ ገዳማዊ መጣዕ ዘሊባኖስ ኢትዮጵያዊ።

፬ ባለምሥራቹ ዮሓንስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት፡፩ዱ።

፮ ኖኅ † ዕርገተ ኤልያስ።

፯ የአስተርእዮ ቅድስት ሥላሴ።

፲፪ ድንግል ማርያም፡እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት፥ልጇም ኢየሱስ፡ እውነተኛው መሲሕ መኾናቸው፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል ተገለጠ።

፲፫ ሕንደቄ ንግሥተ-ኢትዮጵያ፡ በ፴፬ ዓ.ም. በጃንደረባዋ አማካይነት፡ ክርስትና ወዳገርዋ መጣ።

፲፬ እንበረም ሊቀ-ካህናት ዘአኵስም በ፫፻፳፭ ዓ.ም. የቅድስት ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ ሥርዓተ ቤተ መቅደስ አሟላ።

፲፭ ቅዱስ ቂርቆስ፡ የ፫ ዓመት ሕፃን ሰማዕት።

፲፮ ቅድስት ኢየሉጣ ሰማዒት፣ የሕፃኑ ቂርቆስ ሴት ወላጅ።

፲፯ ቅዱስ እስጢፋኖስ እንደመምህሩ፡ኢየሱስ መሲሕ፡ለእውነት፡ በይፋ መስክሮ የተሠዋ ቀናዒ ካህንና ቀዳሚ ሰማዕት።

፲፰ ዝርወተ ዐፅሙ ለጊዮርጊስ።

፳፩ የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት፡ወደገነት።

፳፯ ዕርገተ-ኄኖክ።

፳፰ የበዓለ ኢትዮጵያ መግቢያ።

፳፱ በዓለ ኢትዮጵያ።

፴ የበዓለ ኢትዮጵያ ማብቂያ።

ሙሴ፡ከግብፅ፡ በስደት፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ ስለኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር ተምሮ፡ ካመነ በኋላ፡የካህኑን ሴት ልጅ፡ ሲጳራን አገባ፤ የኦማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ተገልጾለት፡ ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ፡ ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ፡ እውን ኾኗል። ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም፡ የኋላ ኋላ፡ በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር፡ ከእስራኤል ሕዝብ፡ በደል እንደደረሰበት ተጽፏል። ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ፡ ገና፡ በምድረ-በዳ ሠፍረው ሣሉ፡ ጽላተ-ሕጉንና ታቦቱን ከእግዚአብሔር ከመቀበሉ በፊት፡ የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን፡ ለእግዚአብሔር በማቅረብ፡ ሥርዓተ-ክህነትን፥ ስለሕዝብ ኣስተዳደርና ስለፍትሕ ኣሰጣጥም በማስተማር፡ የኢትዮጵያን እግዚአብሔራዊ ሥርዓተ-መንግሥት፡ ኣማቱ፡ ኢትዮጵያዊው ዮቶር፡ ለሙሴና ለአሮን፥ ለሕዝቡ ሽማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቧል። (ዘጸአ. ፫፥ ፩-፭፤ ፲፰፥ ፩-፳፯። ዘኍል. ፲፪፥፩-፲፭።)

| የጥር ወር ምንባብ፡- | መጽሓፈ ኢዮብ እና የማቴዎስ ምሥራች። |
|---|---|

## ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Yekkatit (Feb.-Mar., 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | ፩ 8 | ፪ 9 | ፫ 10 | ፬ 11 |
| ፭ 12 ዘወረደ(ቅበላ) | ፮ 13 ዓቢይ ጾም | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 |
| ፲፪ 19 ቅድስት | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23 ኪዳነ-ምሕረት | ፲፯ 24 | ፲፰ 25 |
| ፲፱ 26 ምኩራብ | ፳ 27 | ፳፩ 28 | ፳፪ 1 | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 |
| ፳፮ 5 መጻጉዕ | ፳፯ 6 | ፳፰ 7 | ፳፱ 8 | ፴ 9 | ማስታወሻ፡- | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

፩ ስለመቅዶንዮስ ኑፋቄ፡የ፻፶ ሊቃውንት ጉባኤ በቊስጥንጥንያ።

፫ የግሼን ማርያም አምባ፡በ፲፭፻፴፪ ዓ.ም.በአሕመድ ግራኝ ጦር ተመዘበረ።

፬ ጣይቱ ብጡል፣ ብርሃን ዘኢትዮጵያ።

፮ ማርያም እንተ ዕፍረት፣መሲሕን በእንባዋ እግሩን ያጠበች።
† የዓቢይ ጾምና የጾመ ሕርቃል መግቢያ።

፲ ያዕቆብ ወልደእልፍዮስ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።

፲፪ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን ጦር በሰላማዊው የዓዲስ አበባ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግድያና ዕልቂት።

፲፫ የኢየሱስ መሲሕ የአርባ ቀን ጾም መነሻ።

፲፮ ኪዳነ ምሕረት፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ መሲሕ የተገኘ † የቅዱሱ ኪዳን ጥበቃ፡በ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. የጎግ ማጎግ የሱማሌ ወረራ ካራማራ ድል ላይ በገሃድ ታየ።

፲፰ አዝማቹ ደገልሓን፣ የአሕመድ ግራኝን ጦር፡ በቆራጥነት የተዋጋ ጀግና ኢትዮጵያዊ።

፳፩ ከጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ፱፻፴፫ ዓ.ም. በአገዉ (በዛጔው) መርሓ-ተክለ ሃይማኖት፡ የኢትዮጵያ መልከ ጼዴቃዊ ሥርዓተ- መንግሥት ተመለሰ።

፳፫ ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት፡ የአድዋ ድል።

፳፯ ግራኝ አሕመድ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. ድል ኾነ።

"ይሁዳ፡ ዕጓለ-አንበሳ! እምኀዘአትከ ዕርግ! ወልድየ! ሰከበከ፤ ወኖምከ፡ ከመ አንበሳ፥ ወከመ ዕጓለ-አንበሳ፡ አልቦ ዘያንቅሐከ። ኢይጠፍእ ምልክና፡ እምይሁዳ፤ ወምስፍና፡ እምአባሉ፣ እስከ አመ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ ሎቱ። ወውእቱ፡ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ። ...ወብዙኃን እለ በከዩ፤ ወአነሂ ምስሌሆሙ፤ እስመ አልቦ ዘተረክበ፡ ዘይደልዎ ይክሥታ፥ ወይርአያ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፡ [እንተ ሀለወት] ውስተ የማኑ፡ ለውእቱ፡ ዘይነብር ዲበ መንበር። ወይቤለኒ፡ አሓዱ፡ እምውስተ እልክቱ [፳፬ቱ] ሊቃናት፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ እምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፣ ከመ ይፍትሓ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፥ ወለማኅተሚሃ!' የይሁዳ አንበሳ ደቦል! ከመደብህ ውጣ! ልጄ! እንደአንበሳ ተኛህ፤ አንቀላፋህም፤ እንደአንበሳ ደቦልም፡ ሊቀሰቅስህ የሚችል የለም። መንግሥት፡ ከይሁዳ፥ የሕዝብ አስተዳደርም፡ ከወገኑ አይወጣም፤ ይህ ሥልጣን፡ የሚጠበቅለትን፣ ለአሕዛብም ተስፋቸው የኾነውን፡ እርሱን እስከሚያገኝበት ጊዜ ድረስ። ...በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ያለችውን መጽሓፍ ሊዘረጋ፥ ሊመለከታትም የሚገባው፡ ማንም ስላልተገኘ፡ ብዙዎች አለቀሱ፣ እኔም ዓብሬአቸው አለቀስሁ። ከእነዚያ [ከ፳፬ቱ] ሊቃናት መካከል፡ አንዱ፡- 'አታልቅስ! እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፣ እርሱም፡ የዳዊት ሥር፡ መጽሓፏን ይዘረጋ ዘንድ፥ ማኅተሟንም ይፈታ ዘንድ፡ <u>ድል ነሥቷል!</u>' አለኝ።" የሚለውን፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር ስለፈጸሙት፡ <u>እውነተኞቹ እስራኤል</u> እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፣፩-፭።)

| የየካቲት ወር ምንባብ፡- | አሪት ዘዳግም፥ ትንቢተ ዮናስና የማርቆስ ምሥራች። |
|---|---|

## ፳፻፲፭ (፯ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Meggabit (Mar.-Apr., 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | | | ፩ 10 | ፪ 11 |
| ፫ 12 ደብረ ዘይት | ፬ 13 | ፭ 14 | ፮ 15 | ፯ 16 | ፰ 17 | ፱ 18 |
| ፲ 19 ገብር-ኄር | ፲፩ 20 | ፲፪ 21 | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 |
| ፲፯ 26 ኒቆዲሞስ | ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 | ፳፫ 1 |
| ፳፬ 2 ሆሣዕና | ፳፭ 3 ሰሙነ-ሕማማት | ፳፮ 4 | ፳፯ 5 | ፳፰ 6 ጸሎተ-ሓሙስ | ፳፱ 7 ስቅለት | ፴ 8 ታላቁ-ሰንበት |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

- ፩ አጼ ዮሓንስ ፬ኛ የመተማው ሰማዕት በድርቡሽ እስላም ወራሪ የተሠየፈ።
- ፭ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳማዊ።
- ፰ ማትያስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።
- ፲፩ ገዳማዊ አሌፍ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ።
- ፳፫ ዳንኤል ነቢይ።
- ፳፬ ሆሣዕና † ንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ።
- ፳፭ የሰሙነ ሕማማት መግቢያ † የሓጋይ (የበጋ)ወራት ማብቂያ።
- ፳፮ የጸደይ (የበልግ) ወራት መግቢያ።
- ፳፯ የአይሁድ ሸንጎ፡ ኢየሱስ መስሕን ለመግደል ወሰነ። † አጼ ገላውዴዎስ፡ ኵትልክናን፡ በተዋሕዶነት የተቋቋመ፣ በእስላም ወራሪ፡ ሰማዕትነትን የተቀበለ።
- ፳፰ ጸሎተ ሓሙስ። † ቈስጠንጢኖስ ቄሣር፡ ስለሃይማኖትና ስለፍትሓ-ነገሥት ዝግጅት፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤን፡ በኒቅያ አሰባሰበ።
- ፳፱ የኢየሱስ መሲሕ መስቀለ-ሞቱ።
- ፴ ኢየሱስ መሲሕ በመቃብር ያረፈባት ታላቋ ሰንበት።

**"'ናሁ ይመጽእ መዋዕል!' ይቤ እግዚአብሔር፣ 'ወአቀውም ለዳዊት፡ ሠርፀ ጽድቅ፤ ወይነግሥ ንጉሥ፡ ዘይኄሊ፣ ወይገብር ጽድቀ፥ ወርትዐ፡ በዲበ ምድር። ...ወይሠርፅ ጽድቅ፡ በመዋዕሊሁ፤ ወብዙኀ ሰላም፡ እስከ የኀልፍ ወርኅ። ወይኴንን እምባሕር፡ እስከባሕር፤ ወእምአፍላግ፡ እስከአጽናፈ ዓለም። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፤ ወጸላእቱሂ፡ ሐመደ ይቀምሑ። ...እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ፡ እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር። ...አንተ ሰበርከ ርእሶ፥ ወቀጥቀጥከ አርእስቲሁ ለከይሲ። ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ።** 'እነሆ፡ ለዳዊት፡ የእውነት ቍጥቋጥ የማስነሣበት ጊዜ ይመጣል! እርሱም፡ በምድር ላይ፡ እውነትንና ቅንነትን የሚያስብና የሚያደርግ ንጉሥ ይኾናል!' ይላል እግዚአብሔር። ...በዘመኑ፡ እውነት ትከሠታለች፤የግብዝነቱም ወራት አልፎ፡ ሰላም ይበዛል። ከባሕር እስከባሕር፥ ከታላላቁ ወንዞች፡ እስከምድር ዳርቻ ያለውን ዓለም ያስተዳድራል። <u>**የኢትዮጵያ ልጆች፡ ዜጎቹ ይኾናሉ**</u>። ጠላቶቹም፡ አፈር ይበላሉ። ...እግዚአብሔርማ፡ ከዓለም አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው! በምድርም መካከል፡ መድኃኒትን አደረገ።...አንተ፡ የአባቡን ራስ ሰበርህ! ራሶቹንም፡ ቀጠቀጥህ! <u>**ለኢትዮጵያ ሕዝብህም፡ ሲሳያቸውን ሰጠሃቸው!**</u>(ኤር. ፳፫፥ ፭። መዝ.፸፩፥፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬)

| የመጋቢት ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ-ኢሳይያስ እና የጳውሎስ መልእክታት። |
|---|---|

# ፳፻፲፭ (፯ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሚያዚያ ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Miazia (Apr.-May, 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበተ ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 9 ትንሣኤ | ፪ 10 ማዕዶት | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13 | ፮ 14 | ፯ 15 |
| ፰ 16 ዳግም ትንሣኤ | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20 | ፲፫ 21 | ፲፬ 22 |
| ፲፭ 23 | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29 |
| ፳፪ 30 | ፳፫ 1 | ፳፬ 2 | ፳፭ 3 | ፳፮ 4 | ፳፯ 5 | ፳፰ 6 |
| ፳፱ 7 | ፴ 8 | ማስታወሻ:- | | | | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

- ፩ የኢየሱስ መሲሕ በዓለ ትንሣኤ።
- ፪ ማዕዶት (በሕይወተ-ሥጋ እያሉ በመንፈስ፡ወደትንሣኤ ሕይወት መሻገር)።
- ፭ ኣዳም ሓሙስ፡ (የ፭ሺ ፭፻ው ዓመት ተስፋ ፍጻሜ) † ሕዝቅኤል ነቢይ።
- ፮ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ኣርበኛው ኣጼ መሪ።
- ፯ ኢትዮጵያዊው ኢያቄም፡ የድንግል ማርያም ወንድ ወላጅ።
- ፰ ዳግም ትንሣኤ (ከፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ በኋላ ያለው የፍጻሜ ትንሣኤ መታሰቢያ።) † ማርቆስ ባለምሥራቹ።
- ፲፪ ደብረ-ብርሃን፡ በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በኣሕመድ ግራኝ ተቃጠለ።
- ፲፫ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ፋሺስት ጣልያን፡ ማኅበረ ሥላሴን፡ በኣየር ኃይሉ ደበደበ።
- ፲፭ ሦስት የማኅበረ-ሥላሴ ገዳም ኣባሎች በ፲፱፻፳፰ዓ.ም. በፋሺስት የጣሊያን ጦር ተገደሉ።
- ፲፯ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ: ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።
- ፳፩ እጨጌ ዕንባቆም ሰባኬ ሃይማኖት።
- ፳፫ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት።
- ፳፭ ርክበ ካህናት።
- ፳፯ ኢትዮጵያ፡ ነጻነቷና በፋሺስት ጣልያን ላይ የተቀዳጀችው ድል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ ተረጋገጠ።

"ወንግሥተ ሳባ፡ ሰምዓት ስሞ ለሰሎሞን፤ ወስሞ ለእግዚአብሔር፤ መጽአት ትፍትኖ፡ ምስለ ጥበባ። ወቦአት ኢየሩሳሌም፡ በኃይል ክቡድ ፈድፋደ።...ወቦአት ኀበ ሰሎሞን፤ ወተናገረቶ ኵሎ ዘሀሎ ውስተ ልባ። ...ወወሀበቶ ለሰሎሞን፡ ምእተ፥ ወዕሥራ መካልየ ዘወርቅ፥ ወአፈዋተ ፈድፋደ ብዙኀ፥ ወዕንቈ ክቡረ፤ ወአልቦ አመ መጽአ ብዙኀ አፈዋተ፡ ዘከመ አሜሃ፡ ዘወሀበት ንግሥተ ሳባ፡ ለሰሎሞን። የሳባ ንግሥት፡ የሰሎሞንን ስም፥ የእግዚአብሔርም ስም፡ በእርሱ ሲጠራ በሰማች ጊዜ፡ ስለሃይማኖቱና ስለእውነተኛ ማንነቱ፡ በጥበቧ ትፈትነው ዘንድ፡ እጅግ ብዙ ከኾነ ሠራዊትና ጓዝ ጋር፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደኢየሩሳሌም መጣች።...ወደሰሎሞንም ገባች፤ በልቧ ውስጥ ያለውን ኹሉ፡ ገልጣ ነገረችው። መቶ ሃያ የወርቅ መክሊትን፥ እጅግ ብዙ የኾነ ሽቱን፥ የከበረ ዕንቍንም [ሉልን] ሰጠችው። የዚያን ጊዜ፡ የሳባ ንግሥት፡ ለሰሎሞን የሰጠችውን፡ ያን የመሰለ ብዛት ያለው ስጦታ፡ ከዚያ ወዲያ አልመጣም።" የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምድር ላይ በተገለጠበት ጊዜ፡ ከእርሱ፡ ማስረጃ ምልክትን ለጠየቀው፡ ለዚያ፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ክፉና ዘማዊ ትውልድ፡ እንዲህ የሚል የመጨረሻ መልስን ሰጠ፡- "ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሖ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ። ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።" ከዚህ ፍርድ ለመዳን፡ "ነገሥተ ምድር ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር! ወዘምሩ ለአምላክነ! ወለኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር። እናንተ፡ በምድር ያላችሁ የሰዎች መንግሥታት ኹሉ፡ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔርና እጆቿን፡ ወደእርሱ አድርሳ ለምትኖረው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘምሩ! ምስጋናችሁንም አቅርቡ!" (፩ነገ. ፲፥ ፩-፲። ማቴ. ፲፪፥ ፴፪። መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፪።)

| የሚያዝያ ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ ዳንኤል እና ራእየ-ዮሓንስ። |
|---|---|

# ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of G'nbot (May-June, 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ 9 | ፩ 9 | ፪ 10 | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13 |
| ፮ 14 | ፯ 15 | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18 ዕርገት | ፲፩ 19 | ፲፪ 20 |
| ፲፫ 21 | ፲፬ 22 | ፲፭ 23 | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 |
| ፳ 28 በዓለ-መንፈስ ቅዱስ | ፳፩ 29 ጾመ-ሓዋርያት | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 | ፳፬ 1 | ፳፭ 2 | ፳፮ 3 |
| ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6 | ፴ 7 | ማስታወሻ:- | | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

፩ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ የመወለዷ መታሰቢያ።

፪ ኢዮብ ጻድቅ ኢትዮጵያዊ።

፭ ኢትዮጵያውያኑ ኤርምያስ ነቢይ፥ ደቀ-መዛሙርቱ፡ አቤሜሌክና ባሮክ።

፮ ሰሎሜ ቅድስት፡ የደብረ ሊባኖሷ ኢትዮጵያዊት።

፱ ዕሌኒ ንግሥት፡ የመሲሕ ኢየሱስን መስቀል አስቆፍራ አስገኘች።

፲ ዕርገት † አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል በሃይማኖታቸው ጽናት፡ ከባቢሎን እሳት ዳኑ።

፲፩ ያሬድ ኢትዮጵያዊው ማሕሌታይ ካህን † ገዳማዊ አሴር፡ የባሌ መምህር።

፲፪ ኣጼ እስክንድር፡ የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል፡ ሰማዕትነትን፡ በወጣትነቱ የተቀበለ † ዮሓንስ አፈወርቅ።

፲፫ የደብረ-ሊባኖስ ገዳም አባሎች፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር ተሠዉ።

፲፭ ናትናኤል፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።

፳ በዓለ መንፈስ ቅዱስ (በዓለ ሃምሳ) † ቅዱስ ኣጼ ካሌብ፡ ወደ ናግራን (የመን) ግዛቱ፡ በመርከብ ዘምቶ፡ የአይሁድን አሠቃቂ ወረራ ድል አደረገ።

፳፩ የሓዋርያት ጾም መግቢያ። † የደርግ፡ የክህደትና የዓመፅ አገዛዝ፡ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተወገደ።

፳፬ ዕንባቆም ነቢይ።

፳፭ ቅድስት ሰሎሜ፡ በሕፃኑ ኢየሱስና በቅድስት ድንግል እናቱ ስደት ያልተለየች።

፳፮ ቶማስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።

፳፯ ያዲስ ኣበባ ሕዝብ ከተቀጣጠሉት የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤቶች፡ የዕልቂት እሳተ ገሞራነት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የከለላ ኃይል ዳነ።

፳፱ ገዳማዊ አፍጼ እና ገዳማዊ ጉባ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፪ቱ።

ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር፡ ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ፡ "ኢትፍትሑ፡ በአድልዎ ገጽ! አላ፡ ፍትሐ-ጽድቅ ፍትሑ! ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ፡ መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" አላቸው። ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ላይ፡የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በሲጳራ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ መሲሕ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ፡ ማስተዋል ነው። "'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ። ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ሲል፡ ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃላት፡ በዚያን ጊዜም፡ አይሁድ ኣላስተዋሏቸውም። (ዮሓ. ፯፥ ፲፬-፳፬። ዘኁል. ፲፪፥ ፩-፲፮። አሞ.፱፥ ፯።)

| የግንቦት ወር ምንባብ:- | መጻሕፍተ አስቴር፥ ምሳሌ እና መክብብ። |
|---|---|

# ፳፻፲፭ (፯ሺ፭፻፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Seney (June-July, 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | | ፩ 8 | ፪ 9 | ፫ 10 |
| ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ 13 | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 |
| ፲፩ 18 | ፲፪ 19 | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23 | ፲፯ 24 |
| ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ 27 | ፳፩ 28 | ፳፪ 29 | ፳፫ 30 | ፳፬ 1 |
| ፳፭ 2 | ፳፮ 3 | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6 | ፴ 7 | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

- ፩ ወንድሞቹ የሸጡት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍና ኢትዮጵያዊት ሚስቱ ኣስናት።
- ፮ በፋሺስት ጣልያን የታጠቀ፣ የተመራም፡ የራያ እስላም፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. የሸዋ ቆላ ኢትዮጵያውያንን፡ በሰለባ ጭምር ፈጀ።
- ፱ ሳሙኤል ነቢይ።
- ፲፪ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ-መላእክት † አጼ ላልይበላል።
- ፲፯ ገዳማዊ ገሪማ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ።
- ፳ ሕንጸታ፡በኣዳምና ሔዋን ኪዳነ ሰብሳብ፡ በኢትዮጵያ የተመሠረተችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ መሲሕ ኪዳነ- ምሕረት: በኢየሩሳሌም ተገለጠች † ኤልሳዕ ነቢይ።
- ፳፩ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና ዓመፅ የፈጸመውን የኢትዮጵያ ትውልድ ሊቀጣ የተላከው ደርግ በ፲፱፻፷፮ዓ.ም.ተቋቋመ።
- ፳፫ ሰሎሞን ንጉሥ፡ የምኒልክ አባት።
- ፳፬ ሙሴ (ጸሊም) ኢትዮጵያዊ።
- ፳፭ ያስቆሮቱ ያይደለ ሓዋርያው ይሁዳ † የጸደይ (የበልግ) ወራት ማብቂያ።
- ፳፮ ኢያሱ ወልደ-ነዌ † የክረምት (የዝናም) ወራት መግቢያ።
- ፳፱ ቀዳማዊ ቴዎድሮስ በሺ፬፻፬ ዓ.ም. የተቀባው ስመ ጥሩው ጻድቅ ኣጼ።
- ፴ የላስታ ላልይበላል [ላሊበላ] አብያተ ክርስቲያን በ፲፭፻፳፭ ዓ.ም. በኣሕመድ ግራኝ ጦር ተበዘበዙ።

"ወነበቦ መልአከ-እግዚአብሔር፡ ለፊልጶስ፤ ወይቤሎ፡- 'ተንሥእ! ወሑር፡ ጊዜ ቀትር፣ ፍኖተ በድው፡ ዘያወርድ፡ እምኢየሩሳሌም፡ ለጋዛ! ወተንሥአ፤ ወሖረ፤ ወረከበ፡ ብእሴ፡ እምሰብአ ኢትዮጵያ፣ ኅፅዋ ለሕንደኬ፡ ንግሥተ-ኢትዮጵያ፥ ወመጋቢሃ ውእቱ፡ ላዕለ ኵሉ መዛግብቲሃ። ወሖረ ኢየሩሳሌም ይስግድ። ወእንዘ ይገብእ፡ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ፤ ወያነብብ፡ መጽሓፈ ኢሳይያስ ነቢይ። ወይቤሎ መንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ።- 'ሑር! ትልዎ፡ ለዝ ሠረገላ!' ...ወይቤሎ ኅፅው፥ ...ወአስተብቍዖ ለፊልጶስ፡ ከመ ይዕርግ፥ ወይንበር ኅቡረ ምስሌሁ። የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፡ 'በቀትር ጊዜ ተነሥተህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ-በዳ መንገድ ኺድ!' ኣለው። ተነሥቶም ኼደ። እነሆም፡ ከኢትዮጵያ ሰዎች የኾነ አንድ ሰውን ኣገኘ። እርሱም፡ 'ሕንደኬ' የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባዋ የኾነ፥ በሀብቷም ላይ ኹሉ የሠለጠነ፡ በዥሮንዷ ነው፤ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ፡ ከተሳለመ በኋላ፡ በሠረገላው ተቀምጦ ሲመለስ፡ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሓፍ እያነበበ ነበረ። መንፈስ ቅዱስም፡ ፊልጶስን፡- 'ኺድ! ይህን ሠረገላ ተከተል!' ኣለው። ...ጃንደረባውም፡ ፊልጶስን ኣናገረው፤ ወደሠረገላው ወጥቶ፡ ከእርሱ ጋር ዓብሮት እንዲቀመጥም ለመነው።" የዓዲስ ኪዳኑ ኣቤሜሌክ የኾነው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ "ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ ኣምናለሁ!" ስላለ፡ ፊልጶስ፡ እዚያው አጠመቀው። ከጥምቀቱም በኋላ፡ ጃንደረባው አቤሜሌክ፡ በተደረገለት፡ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም፡ ዘለዓለማዊ፡ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ በደስታ እጅግ ተመሥጦ ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ከአጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ የመወሰዱን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ። (የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፵።)

| የሰኔ ወር ምንባብ፡- | የሓዋርያት ሥራ እና ንኡሳኑ መልእክታት። |
|---|---|

## ፳፻፲፭ (፸፻፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሓምሌ ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Hamley (July-Aug., 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ 6 | ማስታወሻ፡- | | | | | ፩ 8 |
| ፪ 9 | ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ 13 | ፯ 14 | ፰ 15 |
| ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 |
| ፲፮ 23 | ፲፯ 24 | ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ 27 | ፳፩ 28 | ፳፪ 29 |
| ፳፫ 30 | ፳፬ 31 | ፳፭ 1 | ፳፮ 2 | ፳፯ 3 | ፳፰ 4 | ፳፱ 5 |

### የበዓላትና ኣጽዋማት ማውጫ

- ፪ ታዴዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ።
- ፫ ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (ቄስ) የኣኵስም ንቡረ-እድ፤ የኢትዮጵያ እግዚኣብሔር መንግሥት ምሥክር፡ ልደት።
- ፬ የጾመ ሓዋርያት ማብቂያ።
- ፭ በዓለ ቅዱሳን ሓዋርያት፡ ጴጥሮስ ወጳውሎስ።
- ፮ ዕርገተ እዝራ።
- ፯ ሥሉስ ቅዱስ በኣብርሃም ቤት የተገኙበት † በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር በሰማዕትነት የተሠዉት ፫፻ቱ የደብረ-ሊባኖስ ገዳም ኣባላት።
- ፲፭ ኤፍሬም: የውዳሴ ማርያም ደራሲ።
- ፲፯ ነቢዩ ዮናስ፡ ነነዌ ገባ።
- ፲፰ ያዕቆብ፡ በኢየሩሳሌም፡የቤተ-ክርስቲያን የመጀመሪያው ሊቀ-ካህናትና ሰማዕት † የኢትዮጵያ ልጆች፡ ጦቢያና ጦቢት።
- ፲፱ ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ-መላእክት፡ ሕፃኑን ሰማዕት ቂርቆስንና እናቱን ኢየሉጣን፡ ተጥለውበት ከሚነድድባቸው እሳት ኣዳነ።
- ፳፩ ኣጼ ሠርፀ-ድንግል፡ ሃይማኖታዊው ተጋዳይ።
- ፳፪ ቅዱስ ዑራኤል፡ ሊቀ-መላእክት።
- ፳፫ ቅዱስ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ሰማዕት፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት የጣልያን ጦር፡ በግፍ፡ ተገደለ።
- ፳፬ የደብረ ሊባኖስ ገዳም፡ በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በኣሕመድ ግራኝ ተቃጠለ ከገዳሙ ኣባሎች መካከል፡ እየራሳቸውን፡ ለእሳቱ፡ በሰማዕትነት ማገዱ።
- ፳፭ ገዳማዊ ሕፃን-ሞኣ ኢትዮጵያዊ።
- ፳፮ ጻድቅ ዮሴፍ ኢትዮጵያዊ፡ ሕፃኑን ኢየሱስንና እናቱን ድንግል ማርያምን ለማገልገል በመብቃቱ፡ በፈጣሪ የተመረጠ ጃንደረባ።
- ፴ ማርያም ክብራ (እቴጌ ናዖድ ሞገሳ) የኣጼ ናዖድ ሚስት።

**"ወአንጐርጐሩ አይሁድ በእንቲአሁ፤ እስመ ይቤሎሙ፡- 'አነ ውእቱ፡ ኅብስተ-ሕይወት፤ ዘወረደ እምሰማይ!' ወይቤሉ፡- 'እፎ ይክል ዝንቱ፡ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ?'** እንግዴህ፡ ኢየሱስ፡ 'ከሰማይ የወረደ እንጀራ፡ እኔ ነኝ!' ስላላቸው፡ ኣይሁድ፡ ስለእርሱ ኣንጐራጐሩ፤ 'እንዴትስ፡ ይህ ሰው፡ ሥጋውን እንበላ ዘንድ ሊሰጠን ይችላል?' ኣሉም።" ከዚህ የተነሣ፡ **"ወብዙኃን፡ እምአርዳኢሁ፡ እለ ሰምዑ፡ ወይቤሉ፡ 'ዕፁብ ዝንቱ ነገር! ወመኑ ይክል ሰሚዖቶ? ...ወገብኡ ድኅሬሆሙ፤ ወኢሖሩ እንከ ምስሌሁ።'** ከደቀ-መዛሙርቱ መካከል ሳይቀር፡ ይህን የሰሙ፡ ብዙዎች፡ 'ይህ፡ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው! ማን ሊሰማው ይችላል?' ብለው፡ እርሱን መከተልን ትተው፡ ወደኋላቸው ተመለሱ።" በዚህ ጊዜ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ **"አማን አማን እብለክሙ! እመ ኢበላዕክሙ ሥጋሁ፡ ለወልደ ዕጓለ-እመሕያው፤ ወኢሰተይክሙ ደሞ፡ አልብክሙ ሕይወት ላዕሌክሙ። ዘበልዐ ሥጋየ፥ ወሰትየ ደምየ፡ ቦ ሕይወት ዘለዓለም። ወአነ አነሥኦ፡ በደኃሪት ዕለት።** እውነት እውነት እላችኋለሁ! የማርያምን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን፡ የበላ፤ ደሜንም፡ የጠጣ፡ የዘለዓለም ሕይወት ኣለው። እኔም፡ በመጨረሻው ቀን ኣስነሣዋለሁ።" ሲል፡ ሊድን ለሚፈልግ፡ ለዓለሙ ሰብኣዊ ፍጡር ኹሉ፡ የመጨረሻ ዓዋጅ የኾነውን፡ የእግዚኣብሔርን እውነት፡ ገልጦና ኣስረግጦ ተናገረ። (ዮሓ.፮፥ ፶፩-፶፱።)

| የሓምሌ ወር ምንባብ፡- | ደቂቀ ነቢያት እና የዮሓንስ ምሥራች። |
|---|---|

## ፳፻፲፭ (፪ሺ፲፭) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ነሐሴ ዘመነ ሉቃስ ባለምሥራቹ

2015 Era of Mercy. Month of Nehassey (Aug-Sept., 2023). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሐሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ ጾመ-ፍልሰታ ለማርያም | ፪ 8 | ፫ 9 | ፬ 10 | ፭ 11 | ፮ 12 |
| ፯ 13 | ፰ 14 | ፱ 15 | ፲ 16 | ፲፩ 17 | ፲፪ 18 | ፲፫ 19 ደብረ-ታቦር (ቡሔ) |
| ፲፬ 20 | ፲፭ 21 | ፲፮ 22 ፍልሰተ ትንሣኤሃ ለማርያም | ፲፯ 23 | ፲፰ 24 | ፲፱ 25 | ፳ 26 |
| ፳፩ 27 | ፳፪ 28 | ፳፫ 29 | ፳፬ 30 | ፳፭ 31 | ፳፮ 1 | ፳፯ 2 |
| ፳፰ 3 | ፳፱ 4 | ፴ 5 | ጳጉሜ ፩ 6 | ፪ 7 | ፫ 8 | ፬ 9 |
| ጳጉሜ ፭ 10 | ፮ 11 | ማስታወሻ:- | | | | |

## የበዓላትና አጽዋማት ማውጫ

- ፩ የፍልሰታ ለማርያም ጾምና ሱባዔ መግቢያ † ኢየሱስን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ።
- ፭ ገዳማዊ ፊልጶስ፡ ዘደብረ-ቢዘን
- ፮ ማርያም መግደላዊት፡ የመሲሕን ትንሣኤ፡ቀድማ አይታ አበሠረች
- ፯ አጼ ናዖድ የመልክዓ ማርያምና የመልክዓ ኢየሱስ ደራሲ።
- ፲፫ ቡሔ ደብረ-ታቦር፡ ጌታ፡ በግርማ መለኮቱ ታየ።
- ፲፬ የፍልሰታ ለማርያም ሱባዔ ማብቂያ።
- ፲፭ የፍልሰታ ለማርያም ጾም ማብቂያ።
- ፲፮ የድንግል ማርያም፡በዓለ ፍልሰታ †ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት በ፳፻፲፭ ዓ.ም. ራሷን በአዋጅ፤ለግዙፉ ዓለም፤በይፋ ገለጠች።
- ፲፰ አዝማች አዳሉ፡ በአሕመድ ግራኝ ወረራ የተሠዋ።
- ፳፫ ገዳማዊ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡ ኢትዮጵያዊው የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት፥ የሌሎችም ጸሎታት ደራሲ።
- ፳፬ እጨጌ ተክለ-ሃይማኖት፤ በ፲፪ኛው ፻ ዓመት፡ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት፡ ወደሰሎሞናዊው አገዛዝ እንዲመለስ ያስማማ † ክርስቶስ ሠምራ፡ ለኢትዮጵያዊነት አብነት።
- ፳፯ አጼ ዓምደ ጽዮን፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተጋደለ።
- ፳፰ አብርሃም፥ ይስሓቅና ያዕቆብ።
- ፳፱ ንዋየ-ክርስቶስ (አለቃ ዘካርያስ)፡እስላም ሣለ እስላሞችን፡ በቁርዓናቸው የረታና ብዙዎቹን፡ ያስጠመቀ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ፡ ለኢትዮጵያዊነት፡ አብነትና ድልድይ የኾነ።
- ፴ መልከ-ጼዴቅ፡እርሱም ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኖኅ የተረከበው የፊተኛው፤አብርሃምን በባረከው፡ በማእከላዊው አማካይነት፡ ለመጨረሻውና ለአማናዊው ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ኢየሱስ መሲሕ ቀዳሚ አርአያ የኾነው።

### ጳጉሜ

- ፩ የንስሓ ጾም መግቢያ።
- ፫ ቅዱስ ሩፋኤል † አጼ ዘርዓ ያዕቆብ።
- ፬ የቅዱሳንና የቅዱሳት ኹሉ ዝክር።
- ፭ ዓሞጽ ነቢይ።
- ፮ የንስሓ ጾም ማብቂያ።

መልአኩ፡ ቅዱስ ገብርኤል፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻትን፡ ድንግል ማርያምን፡ "**ተፈሥሒ ፍሥሕት፡አ ምልዕተ-ጸጋ፡ እግዚአብሔር ምስሌኪ! ቡርክት አንቲ እምአንስት!** ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽው፥ እግዚአብሔርም፡ ካንቺ ጋራ የኾነው፡ አንቺ፡ ጸጋን የተመላሽ፡ ደስተኛዪቱ ሆይ! ደስ ይበልሽ!" አላት። መንፈስ ቅዱስ የመላባት ኤልሣቤጥም፡ "**ቡርክት አንቲ እምአንስት! ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ!** ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ አንቺ የተባረክሽ ነሽ! የማሕፀንሽም ፍሬ፡ የተባረከ ነው!" አለቻት። ራሷ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ "**ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ! እስመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ! ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ!** እስመ ገብረ ሊተ፤ ኃይለ ዐቢያተ! ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ ታልቀዋለች! መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል! የአገልጋዩን መከራ አይቷልና! እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ ያመሰግኑኛል! እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና። (ሉቃ. ፩፥ ፳፮-፶፱።)

| የነሓሴ እና የጳጉሜ ወራት ምንባባት:- | መጽሓፈ ጦቢት እና የሉቃስ ምሥራች። |
|---|---|